ቀን፤ <u>መስከረም 27፤ 2012</u>

# የአቶ ሽመልስ የተሠባሪ/ሠባሪ ንግግር ጸረ መደመር ነው! አያሻግርም!

## የፖለቲካ ሹመኞች በባሕላዊ/ሃይማኖታዊ መድረኮች ንግግር ከማድረግ መታቀብ አለባቸው

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ፤ የአገራችን ኢትዮጵያ ኅብረብሔራዊነት መገለጫ ከሆኑት አንዱ የሆነው የኢሬቻ በዓል በሰላም በመጠናቀቁ በቅድሚያ ለጨዋው ሕዝባችን ከፍ ያለ ምስጋና ለማቅረብ ይወዳል። በተለይም ለበዓሉ ክብር በማለት ለሁለት ቀናት ያህል ብዙ መስዋዕትነት ለከፈለውና ከየክፍለ ሃገሩ ለመጡ ታዳሚዎች የሚችለውን በማድረግ ዕገዛ ላደረገው ጨዋው የአዲስ አበባ ሕዝብ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። ብዙ ክፉ ሃሳቦችና ውጥኖች ሲወሩበት የነበረው በዓል በኢትዮጵያውያን መልካምነትና በሕግ አስከባሪዎች ታታሪነት ያለ አንዳች ችግር መጠናቀቁ አሁንም ሕዝብ አብሮነትን፤ ሰላምን የሚፈልግ መሆኑን በድጋሚ ያረጋገጠበት ነው።

ሆኖም ይህንን በሰላማዊ መንገድ የተጠናቀቀ ታላቅ ክብረበዓል የሚያጠለሽ ተግባር በዚያኑ ዕለት መፈጸሙ የጋራ ንቅናቄችን ይህንን መግለጫ እንዲወጣ ያስገደደው ምክንያት ሆኗል። በዕለቱ ከቀረቡ በርካታ የሚያንጹና አገራዊ አንድነትን የሚያጎለብቱ ንግግሮች መካከል በለውጥ አራማጅነት ከሚጠቀሱትና በምክትል ርዕሰ መስተዳድርነት ከተሾሙ ጀምሮ ተስፋ የተጣለባቸው አቶ ሽመልስ አብዲሣ "ተሠባሪና ሠባሪ" በማለት ያቀረቡት ንግግር ደረጃውን ያልጠበቀ ብቻ ሳይሆን በ"መደመር" እሳቤ በተጀመረው ለውጥ ላይ ጥቁር ነጥብ የጣለ ሆኖ አግኝተነዋል።

በ1985ዓም መለስ ዜናዊ ይመሩት የነበረው የነጻ አውጪ ግምባር (ህወሓት) የአገር ሥልጣን ከተረከበ ብዙም ሳይቆይ መለስ ወደ ትግራይ ሄደው ያደረጉት ንግግር ሞተውም ስማቸውን በክፉ እንዲነሳ የሚያደርግ ሆኖ ቀርቷል። <u>"እንኳዕ ካባኹም ተፈጠርና" ነበር በትግሪኛ ያሉት መለስ ዜናዊ፤ "እንኳን ከእናንተ ተፈጠርኩ"</u> በማለት የተናገሩ ሲሆን በመቀጠልም ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያዋርድ የትግራይን ደግሞ ከፍ በሚያደርግ የንግግር ስልት መርዝ ረጭተው በማለፍ እንኳን ካንተ ተፈጠርኩ ያሉትን ሕዝብ ለራሳቸው የፖለቲካ መጠቀሚያ አድርገውት ቆይተዋል፤ አሁንም ድረስ የዘለቀው የዚሁ ንግግር ውጤት እንደሆነ በብዙ መልኩ ይታያል።

በመስቀል አደባባይ መስከረም 24፤ 2012ዓም በተደረገው የኢሬቻ ክብረበዓል ላይ አቶ ሽመልስ አብዲሣ "የኦሮሞ ሕዝብ እዚህ ፊንፊኔ ነው የተሰበረው፤ ከዚህ ነው ውርደቱ የጀመረው፤ እዚህ ነው ቅስሙ የተሰበረው፤ እነቱፋ ሙና እና ሌሎች የጊዜው ታጋዮችን የነፍጠኛው ሥርዓት እዚህ ነበር የሰበራቸው፤ ዛሬ የሰበረንን ሰብረን፣ ከሥሩ ነቅለን፣ ኦሮሞ በተዋረደበት ቦታ ተከብሯል፤ ኦሮሞ እንኳን አሸነፍክ!" በማለት ያቀረቡትን ንግግር የጋራ ንቅናቄያችን <u>"እንኳዕ ካባኹም ተፈጠርና"</u> ከሚለው የመለስ ዜናዊ ንግግር ለይቶ አያየውም። እንዲሁም አገራችን አሁን እየተመራች ካለችበት የመደመር ዕሳቤ ጋር የሚጋጭ ብቻ ሳይሆን ጸረ መደመር ንግግር ነው ብሎም ያምናል። እንደርስበታለን ከተባለው ከፍታ ማድረስ ቀርቶ አሁን ካለንበትም የሚያሻግር ንግግር አይደለም።

ጉዳዩ ያለው ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩ የተናገሩት ትክክል ነው ወይም አይደለም ከሚለው ሳይሆን ስለ "መደመር" በስፋት በሚሰበክበት ባሁኑ ወቅት ላይ "እንዲህ ዓይነት ሕዝብን በተቃርኖ ውስጥ እንዲገባ የሚደርግ ንግግር ያስፈልጋል ወይ?" የሚለው ነው። ይህንን ዓይነቱን ንግግር በማድረግ ከሚመጣ ጥቅም ባለመናገር የሚደርሰው ጉዳት (የሚደርስም ካለ) አይበልጥም? በተለይ የአብሮነት ተምሳሌት ሆኖ በሚታየውና የዓለም ቅርስ በሆነው የኢሬቻ ክብረበዓል ላይ ደምቆ የወጣውን ሕዝብ እንደዚህ በፖለቲካዊ ንግግር ለግል ጥቅም መጥለፍ አግባብነት አለው? የዛሬ ሦስት ዓመት ለተመሳሳይ ክብረበዓል ወጥተው የቀሩት ወገኖች ደም ሳይደርቅ፤ መታሰቢያቸው በቅጡ ሳይከበር፤ እነርሱ የት ተረስተው ነው አሁን ስለ ተሠባሪና ሠባሪ መደስኮር ያስፈለገው?

አቶ ሽመልስ አብዲሣ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ከመሆናቸው በፊት የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ቢሮ ኃላፊ ነበሩ። በዚህ በኃላፊነት ባሳለፉት የሥልጣን ቆይታ ከኦዲፒ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነታቸው ጋር ተዳምሮ ስለ መደመር በቂ ግንዛቤ ያላቸውና የመርኹ አራማጅ ተደርገው ሊወሰዱ የሚችሉ ናቸው። ወደ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሥልጣን ከመጡ ወዲህም በበርካታዎች ዘንድ ለውጡን በማስቀጠል ትልቅ ተስፋ የተጣለባቸው ነበሩ። በዚህ በራሳቸው አንደበት የ"ዕርቅ" ክብረበዓል ባሉት የኢሬቻ አከባበር ላይ ብሩህ ተስፋ የተጣለበት ወደፊት እያለ ወደ ኋላ ለመጓዝ መምረጣቸው ያስፈለገው ለምን ይሆን? በዚህ ንግግርስ ማንን ነው ለማስቦረቅ የተፈለገው? በከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን ዕርከን ላይ ያለ መሪ በማኅበራዊ ሚዲያ ከተሰለቸው የብሽሽቅ ፖለቲካ ተርታ መሰለፍስ ለምን አስፈለገው?

አገራችን በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ገብታ፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በተደጋጋሚ ታውጆባት፤ የኦሮሞ ልጆችን ጨምሮ በርካታዎች የግፍ ናዳ ሲወርድባቸው በነበረበት ወቅት፤ ኢትዮጵያውያንን ለመከፋፈልና ሕዝቡን እርስበርስ ለማጠፋፋት የተነሱ ኃይሎች "ተሳካልን"

ባሉበት ወቅት ነበር በጎንደር የአንድነትና የአብሮነት የጋራ ንቅናቄ የተጀመረው። **“በጎዳና የሚፈሰው የኦሮሞ ወንድምና እህቶቻችን ደም የእኛም ደም ነው!”** በማለት መፈክር ያነገቡ ደፋሮች ነበሩ ለነፍሳቸው ቅንጣት ሳይሳሱ አውሬውን ፊትለፊት የገጠሙት። በኢሬቻ ክብረበዓል ላይ እንዲህ ዓይነቱን ዘመን ተሻጋሪ በጎነት መዘከር ነው የሚበጀው ወይስ “ተሠባሪ/ሠባሪ” በማለት ሕዝብን ፈጽሞ ለማያስፈልግ መቃቃር ውስጥ መክተት ነው የሚሻለው? አንድ በከፍተኛ አመራር ላይ ያለ ይህንን መገንዘብ እንዴት ይሳነዋል?

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አንድም ኅበረቀለማዊው የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ባልታየበት ክብረበዓል ላይ ከአባ ገዳ የባንዲራ ምልክት ሌላ ባንዲራ ከፍ ብሎ ሲውለበለብ በአደባባይ በታየበት ሥፍራ ላይ ከጥቂት ቀናት በፊት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ምልክት ያለበት የእጅ ጌጥ ያደረጉ ሳይቀር እንዲያወልቁ ሲተጋ የነበረው የሕግ አስከባሪ ኃይል ያልተፈቀደ ባንዲራ አይቶ እንዳላየ ሆኖ ማለፉ መልስ የሚያሻቸው ጥያቄዎችን አስነስቶ አልፏል። በርግጥ በዋዜማው ከባንዲራ ጋር በተያያዘ ፖሊስ ሥርዓትና ደንብ ሲያስከብር ተመልክተናል፤ የበዓሉ ዕለት ግን ይህ ሳይተገበር መቅረቱ ነው ጥያቄ የጫረው።

**ስለዚህ አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት፤ ተዘጋጅተውበትም ይሁን ሳይዘጋጁ፤ በተጽዕኖ ያድርጉት ወይም ራሳቸው አምነውበት፤ ቅቡልነትን ለማግኘት ይሁን ማንአለብኝነት ነድቷቸው፤ አቶ ሽመልስ አብዲሣ በዚህ ንግግራቸው ትልቅ ስህተት ፈጽመዋል ብሎ የጋራ ንቅናቄያችን ያምናል። ይህ ብቻ ሳይሆን በመደመር መርኽ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን ቀጣናውን እንዲያም ሲል አፍሪካን እንታደጋለን ብሎ የተነሳውን የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ የላቀ እሳቤ የሚያኮስስ ብቻ ሳይሆን ጥያቄ ላይም የሚጥል ነው።**

**ለመሆኑ መደመር የማን እሳቤ ነው? የጠ/ሚ/ር ዐቢይና የጥቂት ሰዎች ወይስ የኦዲፒ መርህ? የኦዲፒ ሊቀመንበር የሆኑት ዐቢይ አሕመድ ከአገር ውስጥ እስከ ዓለምአቀፍ መድረክ የሚሰብኩት መደመር በኦዲፒና በተዋረድ ባሉ ኃላፊዎች የማይቀነቀነው ለምንድነው? ፓርቲውና አመራሩ በመርህ ጉዳይ ላይ የት ነው ያሉት? ይህ በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ መታወቅ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው።** ፓርቲውም በእርግጥ የመደመር አቀንቃኝ ከሆነ አፈንጋጮቹን አደብ ሊያስገዛና መደመርን የአገራችን አማራጭ መርህ ነው በማለት መደገፍ የሚፈልጉን አንገት ከመድፋት መታደግ ይገባዋል።

ከሠባሪና ተሠባሪ ትርክት ባለፈ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ የሚያስፈልጉ እጅግ በርካታ ጉዳዮች አሉ። **ለሕዝብ የሚታሰብም ከሆነ በእርግጥ መሰበር ያለባቸው ድህነት፣ ሥራዐጥነት፣ ጭቆና፣ ግፍ፣ መድልዖ፣ መፈናቀል፣ ወዘተ ናቸው።** እነዚህንና መሰል የኅብረተሰባችንን ህጸጾች ተባብረን መስበር ይገባናል። **ከዚህ ባለፈ ግን ምንም ስምምነት የሌለውን ታሪክ እያነሱ ጥላቻንና መቃቃርን በሕዝብ መካከል መዝራት ለመለስ ዜናዊ እንኳን ብዙ ትርፍ ስላላመጣበት ከወዲሁ ሊቀጭ ይገባዋል።**

**ሌላው ልናነሳ የምንወደው ጉዳይ ቢኖር የፖለቲካ ሹመኞች በባህላዊ/ሃይማኖታዊ ክብረበዓላት ላይ ንግግር ከማድረግ እንዲታቀቡ አንድ አገር አቀፍ አሠራር እንዲወጣለት ለማሳሰብ ነው።** የፖለቲካ ተሹዋሚዎች በርከት ያለ ሕዝብ መሰብሰቡን ብቻ በማየት ሕዝብ የተሰበሰበበትን ዓላማ የሚሸር ንግግሮች ሲያደርጉ ሰምተናል። የአቶ ሽመልስ ንግግርም አንዱ ተጠቃሽ ነው። **ስለዚህ የፖለቲካ ሹመኞች በባህላዊ ወይም በሃይማታዊ ክብረበዓል ከመገኘት በስተቀር ንግግር ከማድረግ በሕግ እንዲታቀቡ ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።**

በመጨረሻም የጋራ ንቅናቄያችን **“ከዘር/ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነትን እናስቀድም”** የሚለውን መርህ ሕዝባችን እንዲያጤነው ጥሪ ያደርጋል። **እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ወደፊት ለመቀጠል ያለፈው ላይ ብቻ ሳይሆን የወደፊቱ ላይ የበለጠ ትኩረት ልናደርግ ያሻናል። አገራችንን በዕርቅ፣ ይቅር በመባባል፣ በመከባበር፣ በአንድነት፣ ወዘተ ለመፈወስ የምንፈልግ ከሆነ የኋላውን እየረሳን ወደፊት እንድንመለከት የጋራ ንቅናቄያችን ጥሪ ያደርጋል።**

**ይህ አቶ ሽመልስ ያደረጉትን ዓይነት ለበዓሉም ሆነ ለቀኑ የማይመጥን ንግግር በተመለከተ በአስቸኳይ እርምት እንዲደረግበት የጋራ ንቅናቄያችን ጥሪ ያቀርባል። ከዚህ በተጨማሪም ለእንደነዚህ ዓይነት መቃቃሮች ዋንኛ ምክንያት የሆነውን የጎሣ/የቋንቋ ፌዴራሊዝም ባስቸኳይ ምላሽ የሚያገኝበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል።**

**ለእኛ እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ለመቀጠል በቅድሚያ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን ዋንኛ ጉዳይ ሰብዓዊነት መሆን አለበት። ሰብዓዊነት ወይም ሰው-ነት በመወለድ አይጀምርም፤ በመሞትም አያቆምም! እንደ ሕዝብ ለመለያየትም ሆነ ለመላቀቅ በማይቻል ገመድ ውሉ እስኪጠፋ ተዋህደናል። አንዳንድ ሁኔታዎች አስፈሪና ተስፋ አስቆራጭ ቢመስሉም ከፈጣሪ ጋር በመሆን ወደ ፍጻሜ እናመጣዋለን ብለን እናምናለን። ስለዚህ ከ“ጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነት የቀደመባትን” አዲስ ኢትዮጵያን ለመመሥረት በጽናት እንታገል።**

**ፈጣሪ አገራችንና ድንቅ ሕዝቧን ይባርክልን!**

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ**



ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ በአሜሪካ አገር በትርፍ አልባ የሲቪክ ድርጅትነት በ501 (c) (3) ምደባ ሥር በመካተት በሕግ የተመዘገበ ነው።
በአገር ውስጥም በኢፌዴሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ በቁጥር 4267 ሕጋዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ተቀብሏል። ለተጨማሪ መረጃ
የአኢጋን ዋና ዳይሬክተር **አቶ ኦባንግ ሜቶ** በስልክ ቁጥር፤ 901-742276 ወይም 202-725-1616 ወይም በኢሜል፤
obang@solidaritymovement.org ማግኘት ይቻላል። **የአኢጋን የንግድ ባንክ ሒሳብ ቁጥር፤ 1000289705078 ነው።**